694/2013

## 1. መግቢያ

የመንገድ ትራንስፖርት ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ እድገት የማይተካ ሚና እንዳለው የሚካድ አይደለም። ሚናውንም ደህንነቱ የተጠበቀ ለማድረግ በቴክኖሎጂ የተደገፈና በህግ ማዕቀፍ የሚመራ መሆን ይኖርበታል። ከነዚህም መንገዶች ውስጥ በማንኛውም እንቅስቃሴ የደህንነት መጠበቂያ መሳሪያዎችን መጠቀም ወሳኝ ነው። የአለም የጤና ድርጅት እንዳወጣው መረጃ በህዝብ ትራንስፖርት አማካኝነት የሚንቀሳቀሱ አካላት በጉዞ ወቅት የደህንነት ቀበቶ በአግባቡ ቢጠቀሙ አደጋ በሚያጋጥማቸው ወቅት አሽከርካሪውንና ከፊት የሚቀመጡ አካላት ከ45% እስከ 50% ለሞት ተጋላጭነታቸውን እንደሚቀንስና ከኃላ የሚቀመጡ ተጓዦችን ደግሞ ከ25% እስከ 35% ከሞት ሊታደጋቸው እንደሚችል ያሳያል። በሃገራችንም በደህንነት ቀበቶ አለመጠቀም ምክንያት የደረሱ አደጋዎች ጥናት ተደርጎባቸው የተቀመጡ ባይሆንም ለአደጋዎቹ አስከፊነት የደህንነት ቀበቶን አለመጠቀም ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው የማይካድ ነው።

በአጠቃላይ የደህንነት ቀበቶ ማሰር አሽከርካሪው ወይም ተሳፋሪው አደጋዎች በሚከሰቱበት ወቅት በፊተኛው ወይም በጎን ባሉ የተሽከርካሪው መስታወቶች ተስፈንጥረው እንዳይወጡና በዚህ ምክንያት ይደርስ የነበረውን ከፍተኛ አደጋ ለመቀነስ ከማስቻሉም በላይ አሽከርካሪዎች በአደጋ ወቅት ተሽከርካሪውን ለመቆጣጠር እንዲችሉ ያግዛል በተጨማሪም አደጋ በሚከሰትበት ወቅት አሽከርካሪውና ተሳፋሪዎች ተሽከርካሪው ውስጥ ወይም ከተሽከርካሪው ውጪ ካሉ ግዑዝ ነገሮች ጋር ከመጋጨት እንደሚታደግ ይታመናል።

በመሆኑም በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክን ለመቆጣጠር የወጣ የሚኒስትሮችም/ቤት ደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 3 ከ ሀ እስከ ሐ እንዳስቀመጠው ማንኛውም አሽከርካሪ በፊደል ተራ "ሀ" ከሞተር ብስክሌት በቀር የደህንነት ቀበቶ ሳያስር በመንገድ ላይ ማንኛውንም ተሽከርካሪ ማሽከርከር እንደሌለበት፤ በፊደል ተራ "ለ" ማንኛውም አሽከርካሪ በሚያሽከረክርበት ወቅት በተሽከርካሪው ውስጥ የተሳፈረው ሰው የደህንነት ቀበቶ ማሰሩን ማረጋገጥ እንዳለበ እና በፊደል ተራ "ሐ" ድንጋጌው ተፈፃሚ የማይሆንባቸው ተሽከርካሪዎችን በሚመለከት ባለስልጣኑ ይሆናል ይላል። በደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 3 ከፊደል ተራ "ሀ - ለ" የተደነገጉትን ሳይተገብር ተሽከርካሪን ያሽከረከረ በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብን ለማሻሻል በወጣው የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 395/2009 ሠንጠረዥ "ለ" 4ኛ እርከን ሰንጠረዥ "ሀ" መሰረት ለጥፋቱ የሚመዘገብ ነጥብ 3 ሆኖ 250 ብር እንደሚቀጣ ተደንግጓል። ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች ተግባራዊ ለማድረግና የደህንነት ቀበቶ ባለማሰር ምክንያት የሚደርሰውን አደጋ ለመከላከልና ለመቀነስ ባለስልጣን መስሪያቤቱ ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

694/2013

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የተሽከርካሪ የደህንነት ቀበቶ በተሽከርካሪው ወንበሮች ላይ እንዲኖር እና ተግባራዊ እንዲደረግ የወጣ መመሪያ ቁጥር 694/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

በመመሪያው ውስጥ የቃሎቹ ትርጉም እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

2.1. **ባለስልጣን** ማለት የፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን ማለት ነው፡፡

2.2. **ደንብ** ማለት የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 208/2003 እና የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ(ማሻሻያ) ደንብ ቁጥር 395/2009 ነው፡፡

2.3. **የትራንስፖርት ቢሮ** ማለት ትራንስፖርትን ለመምራት ስልጣን የተሰጠው የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት የሚመራ አካል ነው፡፡

2.4. **የሚመለከተው አካል** ማለት የደህንነት ቀበቶ በተሽከርካሪው ላይ እንዲኖር ለመፍቀድ በህግ ስልጣን የተሰጠው ወይም ውክልና ያለው አካል ነው፡፡

2.5. **የደህንነት ቀበቶ ማለት፡-** በተሽከርካሪ ወንበሮች ላይ የተገጠመ ቀበቶ ሆኖ የአሽከርካሪውንና የተሳፋሪዎችን ወገብ እና/ወይም ትከሻ ከተሽከርካሪው ወንበር ጋር በማቆራኘት በአደጋ ጊዜ አሽከርካሪው ወይም ተሳፋሪው ለጉዳት በቀላሉ እንዳይጋለጥ የሚረዳ ቀበቶ ነው፡፡

### 3. የተፈፃሚነት ወሰን

1. ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ውስጥ በባለስልጣኑ በሚወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በተመረጡ የመንግስት፣በኢትዮጵያ በኤንባሲዎች በተመዘገቡ ተሽከርካሪዎች እንዲሁም የግል፣ የግል የንግድ ተሽከርካሪዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡
2. በክልል ወይም በከተማ አስተዳደር ለተመዘገቡ ተሽከርካሪዎች ክልሎች ወይም ከተማ አስተዳደሮች ከዚህ መመሪያ ጋር በማይቃረን መልኩ በራሳቸው ነባራዊ ሁኔታ መሰረት በማድረግ መመሪያ በማውጣት ተፈፃሚ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

### 4. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ በተሽከርካሪዎች ላይ የደህንነት ቀበቶ እንዲኖር በማድረግ ቀበቶ ባለማሰር በአሽከርካሪዎችና በተሳፋሪዎች ላይ የሚደርሰውን የከፋ የመንገድ ትራፊክ አደጋ መቀነስ ነው፡፡

የትራንስፖርት ባለሥልጣን
አዲስ አበባ
የሬከርድና ማህደር አገልግሎት



እብድዬ የደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

# ክፍል ሁለት

# የተለያዩ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

5. **የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ኃላፊነት**

5.1. በሃገሪቱ የሚገኙ ተሽከርካሪዎች አይነት እና መጠን ያማከለ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የደህንነት ቀበቶ ዲዛይን መስፈርት እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

5.2. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የደህንነት ቀበቶ አጠቃቀም ስርዓትን ለመንገድ ተጠቃሚዎች ያስተዋውቃል፡፡

5.3. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተመረጡ የመንግስት፣ የህዝብ፣ የግል መጠቀሚያ እና የጭነት ተሽከርካሪዎች ላይ ለአሽከርካዎችና ተሳፋሪዎች የደህንነት ቀበቶ ያላቸው ወንበሮች ብቻ መሆን እንደሚገባቸው የቅድመ-ተከተል  መርሐ ግብር ያወጣል ፡፡

5.4. የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተሽከርካሪ ማስገቢያ ሰነድ ላይ በጉምሩክ በኩል ወደሃገር የሚገቡ ተሽከርካሪዎች በሁሉም ወንበሮች ላይ በአምራች ፋብሪካው ወይም ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ባወጣው ዲዛይን እና ደረጃ የደህንነት ቀበቶ ያላቸው መሆኑን ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

5.5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 መሰረት ቁጥጥር ሲያደርግ  ስህተት የተገኘበት ተሽከርካሪም በመመሪያው መሰረት ማስተካከያ እንዲደረግበት  ይቆጣጠራል፡፡

5.6. ተሽከርካሪዎች አመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ሲያደርጉ በአምራች ድርጅቱ በተገጠመላቸው ወንበር ልክ ፋብሪካው ወይም ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ባወጣው ዲዛይን እና ደረጃ የደህንነት ቀበቶ መኖር አስገዳጅ መሆኑን መመሪያ ይሰጣል፡፡

5.7. የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት ለተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ምርመራ ሲያደርጉ የደህንነት ቀበቶ መስራቱን እንዲያረጋግጡ  ያሳውቃል፡፡

5.8. የባለስልጣን መ/ቤቱ በተሽከርካሪዎች ላይ የተገጠመው የደህንነት ቀበቶ በወጣለት መስፈርት ልክ መሆኑን እና በተገቢው አጠቃቀም መፈጸሙን ይቆጣጠራል፡፡

5.9. የደህንነት ቀበቶ አተገባበር ቁጥጥርን በተመለከተ ባለስልጣኑ በህግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት እንደአስፈላጊነቱ በውክልና ወይንም በቅንጅት የሚከናወንበትን መንገድ ይነድፋል፡፡

5.10. በሁሉም የሃገሪቱ ክፍል የደህንነት ቀበቶ አተገባበር ወጥነት ባለው መልኩ እየተከናወነ መሆኑን ይከታተላል፤ ለአፈጻጸሙ መሳካትም ድጋፍ ያደርጋል፡፡

6. **የትራንስፖርት ቢሮ ሃላፊነት**

6.1. ይህንን መመሪያ መሰረት በማድረግ በሚወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ነባር ተሽከርካሪዎች በሚወጣው መስፈርት ለሁሉም ወንበሮች የደህንነት ቀበቶ እየገጠሚ መሆኑን ይከታተላል፤ያረጋግጣል፡፡

6.2. በትራንስፖርት ቢሮዎቹ የኦፕሬሽን ፍቃድ የሚሰጣቸው የመካከለኛ እና አነስተኛ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ለሙሉ መንገደኞች እና ሰራተኞች የደህንነት ቀበቶ እንዲገጥሙ ይቆጣጠራል ይከታተላል፡፡

6.3. የደህንነት ቀበቶ አተገባበርን በተመለከተ ቁጥጥር  ያከናውናል፡፡

6.4. ማንኛውም አሽከርካሪ በሚያሽከረክርበት ወቅት በተሽከርካሪው ውስጥ የተሳፈረው ሰው የደህንነት ቀበቶ ማሰሩን ማረጋገጥ አለበት፡፡

6.5. የፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን ያወጣውን መመሪያ መሰረት በማድረግ የክልል በትራንስፖርት ቢሮዎቹ የደህንነት ቀበቶ አተገባበር የአፈጻጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

6.6. የትራንስፖርት ቢሮዎች በደህንነት ቀበቶ አተገባበር መመሪያ እና አፈጻጸም ዙርያ ለአሽከርካሪዎች፣ ለመንገደኞች፣ ለትራንስፖርት ማህበራት፣ ለተሽከርካሪ ባለንብረቶች፣ ለትራንስፖርት ተቆጣጣሪ አካላት እንዲሁም ለማንኛውም ትራንስፖርት ተጠቃሚ ግንዛቤ ይፈጥራል፡፡

7. **የፌደራል እና የክልል ትራፊክ ተቆጣጣሪ ፖሊስ ኃላፊነት**

7.1. የደህንነት ቀበቶ አተገባበርን በተመለከተ ቁጥጥር ያከናውናል፡፡

7.2. ማንኛውም አሽከርካሪ በሚያሽከረክርበት ወቅት በተሽከርካሪው ውስጥ የተሳፈረው ሰው የደህንነት ቀበቶ ማሰሩን ማረጋገጥ አለበት፡፡

7.3. የደህንነት ቀበቶ አተገባበር ቁጥጥር ስራን በተመለከተ መደበኛ ሪፖርት በየደረጃው ላለው ለትራንስፖርት ቢሮ ወይም ለትራንስፖርት ባለስልጣን አጠናቅረው ያቀርባሉ፡፡

8. **የተሽከርካሪው ባለቤት ኃላፊነት**

8.1. የነባር ወይም የአዲስ ተሽከርካሪ ባለንብረት በአግባቡ የሚሰራ የደህንነት ቀበቶ በተሽከርካሪው ላይ ማሟላት አለበት፡፡

8.2. የደህንነት ቀበቶው በተገቢው ሁኔታ የሚያገለግል መሆኑን በየጊዜው ማረጋገጥ አለበት፡፡

9. **የአሽከርካሪው ኃላፊነት**

9.1. አሽከርካሪው የደህንነት ቀበቶውን በአግባቡ ማድረግና ተሳፋሪዎችም በአግባቡ ማድረጋቸውን በራሱና በረዳቱ በኩል ያረጋግጣል፡፡

9.2. በአግባቡ የሚሰራ የደህንነት ቀበቶ የሌለው ተሽከርካሪ ማሽከርከር የለበትም፡፡

9.3. በአግባቡ የማይሰራ የደህንት ቀበቶ፤ የደህንነት ቀበቶ እንደሌለው ተቆጥሮ እርምጃ ይወሰዳል፡፡

10. **የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት ኃላፊነት**

ማንኛውም የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋም፡-

1. በዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ወቅት የአሽከርካሪውና የተሳፋሪዎች የደህንነት ቀበቶ መኖሩን እና በአግባቡ የሚያገለግል መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

የትራንስፖርት ባለሥልጣን
አዲስ አበባ
የሬከርድና ማህደር አገልግሎት



አብዲሳ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

## ክፍል ሶስት

11. **የደህንነት ቀበቶ የሚገጠምላቸው ተሽከርካሪዎች አይነት**

11.1. ነባር (በስራ ላይ ያሉ) እስከ 150(አንድ መቶ ሃምሳ) ኪሎ ሜትር የሚጓዙ ሚኒባሶች እና የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች፣ ከ5 እስከ 8 መቀመጫ ያላቸው ተሽከርካሪዎች ፣ ረጅም ርቀት የሚገጓዙ ልዩ ባሶችና ሀገር አቋራጭ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች በዚህ መመሪያ ላይ ለአሽከርካሪውና ለሁሉም ተሳፋሪዎች የደህንነት ቀበቶ እንዲኖራቸው የሚወሰን ሲሆን ለግል አገልግሎትም የሚጠቀሙ አውቶሞቢሎች የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ ቦርድ ያለው ማካተት አለባቸው::

11.2. በመመሪያ ቁጥር 3.1 የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ የጭነት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች፣ ከ12 እስከ 15 ሰው የሚጭኑና በከተማ ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ፣ የብዙሃን አገልግሎት የሚሰጡ የከተማ አውቶሶች ለአሽከርካሪውና ፊት ወንበር ላይ ለሚቀመጡ ተሳፋሪዎች የደህንነት ቀበቶ እንዲኖርና እንዲጠቀሙ የሚደነግግ ሲሆን ከኃላ ለሚቀመጡ በብዙሃን ትራንስፖርት ቆመው የሚጓዙ እና አጭር ርቀት የሚጓዙ ተሳፋሪዎች የደህንነት ቀበቶ እንዲኖራቸው አያስገድድም::

11.3. በመንግስትና በግል ለሰራተኞች የሰርቪስ አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎችም በመመሪያው መሰረት ለአሽከርካሪውና ለሁሉም ተሳፋሪዎች የደህንነት ቀበቶ መግጠምና መጠቀም አለባቸው::

11.4. በአስመጪዎች ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ አዲስ የመንግስት፣ የግል፣ የህዝብና የጭነት ተሽከርካሪዎች በባለስልጣኑ መ/ቤት በሚወጣው ስፔስፊኬሽን መሰረት ለአሽከርካሪውና ለተሳፋሪዎች የደህንነት ቀበቶ የተገጠመላቸው መሆን አለበት::

12. **መመሪያው ተፈፃሚ የማይሆንባቸው ተሽከርካሪዎች**

የዚህ መመሪያ ድንጋጌ በባለሁለትና በባለሶስት እግር ተሽከርካሪዎች እንደሁም በግዳጅ ስራ ላይ በተሰማሩ የፖሊሶችና የመከላከያ ሰራዊት ተሽከርካሪዎች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም::

13. **ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች**

የዚህን መመሪያ ድንጋጌ የሚቃረን ማንኛውንም መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ ተፈፃሚነት አይኖረውም::

14. **መመሪያውን ስለማሻሻል**

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለስልጣኑ መመሪያውን ሊያሻሽለው ይችላል::

15. **ቅጣትን በተመለከተ**

በደንብ ቁጥር 395/2009 ሰንጠረዥ እርከን 4 ተራ ቁጥር 9 መሰረት አሽከርካሪው የደህንነት ቀበቶ ሳያደረግ እና ተሳፋሪዎች ማድረጋቸውን ሳያረጋግጥ የሚያሽከረክር ከሆነ ደንቡ ድንጋጌ መሰረት የሚቀጣ ይሆናል ::

16. ይህ መመሪያ ከ 18/02 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትራንስፖርት ሚኒስቴር የትራንስፖርት ባለሥልጣን ቁ.1 Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

አብዲሣ ያደታ
ዋና ዳይሬክተር

አብዲሣ ያደታ ሙሊሳ
ዋና ዳይሬክተር